# ራእይ

# ኢትዮጵያ በ2020 -- ከየት ወዴት?

መስፍን ወልደ ማርያም
ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ማኅበር
ሂልተን፣ ኅዳር 1996

## 1. መግቢያ

ያለንበትን ዓለም አጠቃላይ ሁኔታ መገንዘብ የሚያስፈልግ ይመስለኛል፤ መስከረም 1 ቀን 1993 በአሜሪካ ላይ የደረሰው አስከፊና አረመኔያዊ ጥቃት፣ አሜሪካ ለዚያ መልስ በአፍጋኒስታን፣ ቀጥሎም በኢራቅ የወሰደችው ተመሳሳይ ወታደራዊ እርምጃ፣ በሰሜን ኮሬአ፣ በሶርያና በፋርስ ላይ የምታሰማው ዛቻ፣ የእስልምና አክራሪዎች በሚባሉት በኩልም በኬንያ፣ በኢንዶኒዝያ፣ በኢራቅና በአፍጋኒስታን የሚደረገው ሁሉ በቋፍ ያለውን የዓለም ሰላም እያደፈረሰው ነው። ምናልባትም ለዚህ ሁሉ ጦሱ የፍልስጥኤማውያንና የእሥራኤላውያን መጨረሻው የማይታይና ክፋትና ጭካኔ የተሞላበት ግብግብ ሳይሆን አይቀርም። በአንድ በኩል በማይመጣጠን ኃይል የሚጠቀም ጭቆና ፍልስጥኤማዊነትን ወደአረብነት፣ ከዚያም ወደእስላምነት ሲለውጥ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እሥራኤላዊነትን ወደምዕራባዊነት ወይም ወደአሜሪካንነት እየለወጠ ነው። ስለዚህም የግብግቡ ኢላማ በጣም የሰፋና የተለያየ ሲሆን፣ የግብግቡም መሣሪያ በጣም የተለያየ ሆኖአል። በፍልስጥኤማውያኑና በደጋፊዎቻቸው በኩል ኢላማው የአሜሪካን ወገን የሆነ ሁሉ፣ የአሜሪካ ንብረት የሆነ ሁሉ፣ ለአሜሪካ ጥቅም የዋለ ነገር ሁሉ ነው። በአሜሪካና በእሥራኤል በኩል ኢላማው ሽብርተኛ የሚሉት ነው። ለቀረው የዓለም ሕዝብ በሁለቱም ወገን የሚሰጠው ምርጫ የኔ ወገን ካልሆንህ የጠላት ወገን ነህ የሚል ነው፤ የውጊያውም ዓይነት ከዚህ በፊት በዓለም ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ነው፤ የጦር ሜዳውም ያልተወሰነና ዓለምን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው፤ የጦር መሣሪያውም እንደሰማይና እንደመሬት የተለያየ ነው። የአሜሪካና የእሥራኤል የጥቃት መሣሪያ ዘመኑ ያስገኘው ደፍጥጦ የሚያንድድ ነው፤ የተቃዋሚዎቹ የጥቃት መሣሪያ የሰው ልጅ ሕይወት ነው።ከሁለቱም ወገን በየሳምንቱ የብዙ ሰው ሕይወት እየጠፋና ብዙ ንብረትም እየወደመ ነው። በሁለቱም በኩል

በግልጽ አይሎና አመዝኖ የሚታየው ርኩስ መንፈስ  እንጂ ቅን ወይም ቅዱስ መንፈስ አይደለም።

በአለፈው የፈረንጆች ምዕተዓመት ተከብረው የቆዩ ቁምነገሮች እየተሻሩ ናቸው፤ የአንድ አገር ሉዓላዊነት በኃያላኑ ፈቃድ ብቻ የሚገኝ ሆኖአል፤ ዩጎዝላቪያ፣ አፍጋኒስታን ኢራቅ የደረሰባቸውን እናውቃለን፤ በሰሜን ኮሬአና በኢራን፣ እንዲሁም በሶርያ ላይ የሚሰነዘረው ዛቻና ያንዣበበውም ስጋት ይህንኑ የሚያመለክት ነው። የመረጣችሁትን መሪ ለውጡ የሚል ትእዛዝ ለአንድ ሕዝብ ማስተላለፍ በአሜሪካ ተጀምሮ አሁን አልቃይዳም የራሱን ትእዛዝ እያስተላለፈ ነው። በአጠቃላይ ሲታይ በብዛት ሰዎችን መግደልና ንብረትንና የልማት መዋቅሮችን ማውደም የጉልበተኞች ብቻ ሳይሆን የደካሞችም ዘዴና መብት እየሆነ ነው። የመንፈስ ልዕልና እንኳን በዓለማዊው ክፍልና መንፈሳዊ በሚባለውም ክፍል ክፉኛ ዘቅጦአል። አካላችንን ብቻ ሳይሆን ነፍሳችንንም ለገንዘብ የምንሸጥበት ጊዜ ነው፤ የሰው ልጅ ኩራትና ክብር ዋጋ አጥተዋል። ዓለማችን ለእኔ ይህንን ይመስላል፤ መናጢ ደሀዎችና ደካሞች ሆነን ያለነው እዚህ ዓለም ውስጥ ነው።

ያለንበት የዓለም ሁኔታ በአጠቃላይ ለጭቆና አገዛዝ የማይመች የሚመስል ዝንባሌ ቢኖረውም ኃያላኑ የጭቆና አገዛዞችን በአሽከርነት ለማሳደርም ዝንባሌ እንዳላቸው ይታያል። የምዕራባውያን ዋናው የሽብርተኞች ችግር ከጭቆና አገዛዝ ጋር ያላቸው መቆራኘት መሆኑን ገና የተገነዘቡት አይመስልም፤ የጭቆና አገዛዝ እስካለና ሰላማዊ የፖሊቲካ ትግል እስከታፈነ ድረስ ዓመፅና ሽብርተኛነት ይኖራል፤ የዓመፅና የሽብርተኛነት ኢላማም ከጭቆና አገዛዙ በስተጀርባ ያለውን ድጋፍም እንደጠላት እየቆጠረ ማጥቃቱ የማይቀር ይሆናል። አሜሪካ የሽብርተኞች ኢላማ የሚሆንበት ሌላ ምክንያት አለ ብዬ አላምንም። የአሜሪካ ታሪካዊ ተልእኮዎች -- ነጻነት፣ የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ወይም ዴሞክራሲ፣ ትክክለኛ ፍትሕና የንብረት ማፍራት መብቶች ለሰው ልጆች ሁሉ የሚበጁ ቢሆኑም የአሜሪካ መንግሥት የማያወላውል አቅዋም ሆነው የውጭ ግንኙነት መመሪያው አላደረጋቸውም፤ እንዲያውም የአሜሪካ መንግሥት በተለያዩ ምክንያቶች የጨቋኞች ወዳጅና ደጋፊ አየሆነ ይገኛል። ችግሩ ይህ ይመስለኛል።

በምዕራባውያን ሕዝቦችና በሌሎቻችን መሀከል ያለው ልዩነት እየገዘፈና እየጠለቀ በመሄድ ላይ ነው። ሌሎቻችን በአራት ሺህ ዓመታት ያልደረስንበትን እነሱ በአራት መቶ አልፈውት መሬት እየጠበበቻቸው ወደሕዋው እየመጠቁ ነው፤ እኛ አህያ እየነዳን

በቀን ሰባት ኪሎሜትር ስንገሰግስ እነሱ በሰዓት ብዙ ሺህ ኪሎሜትሮች በመንፈላሰስ እየተጓዙ ነው፤ እኛ ጉልሁንና ግዙፉን ነገር ማየት ሲሳነን እነሱ በዓይን የማይታየውን ሁሉ እያዩና እየመረመሩ ነው፤ እኛ እነሱ የሠሩትን መሣሪያ እየገዛን ስንከሳከስና ሞትን ስናነግሥ እነሱ የሕይወትን ሙሉ ጣዕም እየተደሰቱበት ነው፤ እኛ በጠባቡ በአገራችን ውስጥ አብሮ መኖር ሲያቅተን እነሱ ሰፊውን ዓለም በግድም በውድም አገራቸው እያደ ረጉት ነው፤ እኛም ያጠፉነውን አገራችንን እየጠላን ወደነሱ አገሮች መሰደዱን ባህላችን አድርገን ይዘነዋል። ገና ሳልተሰደድነውም ቢሆን ከአገዛዙ ሥርዓት ጀምሮ እስከግብረ ሠናይ ድርጅቶችና ማኅበሮች የምንንቀሳቀሰው በእነሱ ችሮታ ነው። ከእነሱ ችሮታ ውጭ ያለን ህልውና ዋስትና የለውም።

እንግዲህ ጥያቄው ምን አለን? ብቻ አይደለም፤ ምንድን ነንም ነው።

## 2. የዓለምና የአካባቢው ሁኔታ በእኛ ላይ ያለው ተጽእኖ

የኢትዮጵያዊነትን ህልውና የሚፈታተነው የውስጥ አመራር ብቻ ሳይሆን የውጩም ነው፤ ታሪክ ጠባሳን ይተዋል፤ የተለያዩ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎችን በተለያየ ጊዜ የኢትዮጵያ አልበገርነት አሳፍሮአቸዋል፤ አሜሪካም ቢሆን ይህንኑ አልበገርነት አይቶአል፤ እንዲሁም ቱርክ፣ ግብፅና አረቦች በተለያየ መንገድ የኢትዮጵያዊነትን አለመበገር የተረዱበት ሁኔታዎች አጋጥመዋቸዋል። ጎረቤቶቻችን ከሆኑት ጋር ግን የሚያያይዘን የደምም፣ የባህልም ማኅተም በሁለታችንም ላይ እንደቀረ አያጠራጥርም፤ አንዱና ዋናው ማኅተም እስልምና ነው። እስልምና እንደሃይማኖት አረብ የሆነውን ያህል ኢትዮጵያዊም ነው። ከክርስትናና ከእስልምና በፊት ኢትዮጵያዊነት ከአይሁድነት ወይም ቤተ እሥራኤልነት ጋር ግንኙነት ነበረው። በእኔ አስተያየት አይሁድነትም፣ ክርስትናም፣ እስልምናም በተለያየ ጊዜ ኢትዮጵያዊነትን ለመተካት ሞክረዋል፤ አንዳቸውም አልሆነላቸውም፤ ኢትዮጵያዊነትን በመተካት ፈንታ ሁሉም ኢትዮጵያዊነትን ተጎናጽፈው ኢትዮጵያዊ ሆኑ። ኢየሩሳሌም ለሦስቱም ሃይማኖቶች ቅድስት መካን የመሆንዋን ያህል ኢትዮጵያዊነትም ከዚያች መሬት ታሪክ ተካፋይ ነው።

ሦስቱም ሃይማኖቶች ከኢትዮጵያ ውጭ ምእመናን አሉአቸው፤ ስለዚህም ሃይማኖቶቹ በኢትዮጵያና በሌሎች አገሮች መሀከል እንደድልድይ ሆነው በማገልገላቸው፣ ሰዎች፣ ሀሳቦችና ባህሎች ተዛምደዋል። ዛሬ ግን አይሁድነት ኢትዮጵያዊነትን አውልቆ

እሥራኤላዊነትን ለብሶአል፤ ይህ ሁኔታ ከሌላው የስደት ጎርፍ ጋር ተዳምሮ ኢትዮጵያዊነትን የማራቆቱ ጉዞ መጀመሪያ እንደሆነ አድርገን ልናየው የምንችል ይመስለኛል፤ ከዚያም በላይ የቤተ እሥራኤል እሥራኤላዊነት በእስልምና ኢትዮጵያዊነት ላይ ምን ተጽእኖ ሊያስከትል እንደሚችል አናውቅም፤ ክርስትናም በጎሠኛነት እየተተራመሰ የኢትዮጵያዊነት የክብር ልብሱ እየተቀዳደደበት ነው፤ እስካሁን ድረስ ጎሠኛነትን ተጋፍጦ በቆራጥነት የተቋቋመው እስልምና ብቻ ነው። በአሁኑ ጊዜ ከእስልምና ወይም እንደሚባለው የእስልምና አክራሪዎች ጋር ምዕራባውያን በያዙት ግብግብ ውስጥ የኢትዮጵያን እስልምና ለማስገባት የሚፈልጉ አይጠፉም። ስለዚህም በውጭ ተጽእኖ ተገፋፍቶ የኢትዮጵያ እስልምና ኢትዮጵያዊነትን ያዳክማል አገሪቱንም ለአደጋ ያጋልጣል የሚል ስጋት ይሰማል፤ አገዛዙ ከሶማልያው አል ኢትሀድ ጋር የሚያደርገው ግብግብ በዚህ በማሳበብ ነው። እንዲህ ያለው የግጭት ምክንያት የኢትዮጵያን እስልምና ኢትዮጵያዊነት እንዳይመርዘው መጠንቀቅ የሚያስፈልግ ይመስለኛል። የክርስትና ኢትዮጵያዊነት በውስጥ አመራር ምክንያት እየተዳከመ ባለበት ጊዜ የእስልምና ኢትዮጵያዊነት ደግሞ በውጭ አመራር ምክንያት ቢዳከም በኢትዮጵያዊነት ላይ የሚደርሰው ጉዳት እንደሚባባስ በበኩሌ አልጠራጠርም። በገንዘብ እየተደለሉ ለምዕራባውያን ሎሌነት ማደር ለአገዛዙ የአጭር ጊዜ ጥቅም የሚያገለግል ቢሆንም ለኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል።

## 3. ከየት ተነሥተን ያለንበት ደረስን?

የአፄ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ለእኛ በጊዜው ወጣቶች ለነበርነው በአጉል ባህል የተተበተበ፣ ኢፍትሐዊ የመሬት ስሪት የሰፈነበት፣ ኋላቀርና አዝጋሚ ነበር። ከሞተ ሠላሳ ዓመታት የሆነውን ሥርዓት ከዚህ በላይ አልወቅሰውም። ሆኖም ከጊዜው ጋር መሄድ ስላቃተውና የ1953 የክብር ዘበኛ ዓመፅ ምንም ሊያነቃውና ሊያስተምረው ባለመቻሉ መጥፎ አወዳደቅ አጋጠመው። ደርግ ከነትንሽነቱና ከነጭካኔው የዘውዱ አገዛዝ እልህ ውጤት ነው።

የዘውዱ አገዛዝ ለኢትዮጵያ አጠቃላይ እድገት ያበረከተው አስተዋጽኦ በጣም ትልቅና ከዚያ ወዲህ ከመጡት ጋር ሊወዳደር የማይችል ነው፤ በተለይ በሦስት ዓላማዎች ላይ በአጭሩ የዘውድ አገዛዙ ያበረከተውን አስተዋጽኦ ላመልክት፤ ----

- በመጀመሪያ በአንድነት ላይ በተለይ ኤርትራን ወደእናት አገርዋ ለመመለስ የተደረገውን ተጋድሎ አምባሳደር ዘውዴ ረታ ምስጋና ይድረሰውና በቅርቡ ለማወቅ ችለናል፤ የዛሬውም የኤርትራ ችግር በዚያን ጊዜ የተፈጠረ መሆኑን ተገንዝበናል፤
- ሁለተኛ፣ የመሬት ስሪቱን ትተን በእርሻ በኩል የተጀመረው እድገት ቢቀጥል ዛሬ ኢትዮጵያ ራስዋን ከመቻል አልፋ የተለያዩ የእርሻ ምርቶችን ለዓለም ገበ ያ ማቅረብ የምትችልበት ደረጃ ላይ ትደርስ ነበር የሚል እምነት አለኝ፤
- ሦስተኛ፣ የዘውድ አገዛዙ በትምህርት በኩል ኢትዮጵያ ራስዋን ወደምትችል በት ደረጃ አድርሶአት እንደነበረ ሁላችንም የምናውቀው ነው።

የትምህርቱን ጉዳይ ትንሽ ዘርዘር አድርጌ ልገልጸው እፈልጋለሁ፤ አፄ ኃይለ ሥላ ሴ ራሳቸው ከየሄዱበት ልጆች በመኪና እያስጫኑ በየትምህርት ቤቱ በአዳሪነት ያስገቡ ነበር፤ ይህ ዕድል ባይኖር ብዙዎቻችን የዘመናዊ ትምህርት በርም አንደርስም ነበር፤ እን ደማስታውሰው በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በአዳሪነት ከገቡት ውስጥ ለምሳሌ ከኦጋ ዴን ሶማሌዎች፣ ከሐረር አደሬዎች፣ ከጎጃም፣ ከጎንደር፣ ከትግራይ፣ ከሲዳሞ፣ከአርሲ፣ ከኤርትራ፣ ከወለጋና ከአዲስ አበባም ዙሪያ የመጡ ነበሩ፤ ፍትሐ ነገሥት 'በፍትሕሰ ኢይትኴነን ወልድ በጌጋየ አቡሁ ወኢአብ በአበሳ ወልዱ' ልጅ በአባቱ ወንጀል ወይም አባት በልጁ ወንጀል አይከሰስም' ያለውን በመከተል የታወቀው ከሃዲ የኃይለ ሥላሴ ጉግሳ  ልጅና የአርበኛው ዐመጸኛ የበላይ ዘለቀ ልጆች ነበሩ። የተፈሪ መኮንን ተማሪዎ ች በዐመጽንበት ጊዜ 'ከየትም ለቃቅመን አምጥተን' በማለት ንዴታቸውን የገለጹት ለዚ ህ ነበር፤ የተናገሩት እውነት ቢሆንም እኛን ማሰከፋቱ አልቀረም፤ ለዚህም ነው ማቴዎስ ጥግነህ  የሚባል ተማሪ 'ጃንሆይ አባቶቻችን ታክስ ይከፍላሉኮ!' ያላቸው።

ይህ ባህላዊ አገዛዝ ከውስጥም ከውጭም ተቆጣጣሪ ኃይሎች ነበሩበት፤ ከውስጥ ኅሊና፣ ከውጭ እግዚአብሔርና ይሉኝታ ነበሩበት፤ ሽማግሌዎችም ነበሩ፤ በተጨማሪም አፄ ኃይለ ሥላሴ ብቻ ሳይሆኑ አሽከሮቻቸውም ጭምር ለየራሳቸው ክብር የሚሳሱ ነበ ሩ፤ ስለዚህም ከውስጣቸውም ከውጭም የሚሰሙት ድምፅ ነበረ። ሆኖም አገዛዝ መማር አይችልምና የ1953 የሰዒረ መንግሥት ሙከራ አገዛዙን ሳይለውጠው ቀረ።

በእኔ ግምት የአፄ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርትን በማስገባ ትና በማስፋፋት በኩል ወደር የሌለው እርምጃን አሳይቶአል፤ ትምህርት በአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርትም በር ለማናቸውም ችሎታውን ላሳየ ደሀ ክፍት ነበር። የልዑላን፣ የመሳፍንትና የመኳንንት ልጆች ከደሀው ልጅ ጋር አብረው እየተማሩ አደጉ። እአአ በ1951 ላይፍ የሚባለው መጽሔት ኢትዮጵያ አንድ መሀንዲስ እንኳን የሌላት ደሀ አገር ነች ብሎ መጻፉ እንዴት እንዳናደደኝ አስታውሳለሁ። ጥሩው ነገር በዚያው ዓመት የከ ፍተኛ ትምህርት ተጀመረ። ያለምንም ጥርጣሬ የአፄው መንግሥት በትምህርት በኩል ኢትዮጵያን ገፍቶ ወደሃያኛው ምዕተዓመት አስገብቶአት ነበር ለማለት ይቻላል። ይህ በጦር ትምህርትም ቢሆን እውነት ነበር፤ በሐረር አካደሚ፣ በደብረ ዘይት ዓየር ኃይልና በምፅዋ የባሕርኃይል የነበረው የመኮንኖች ሥልጠና ሁለገብና በጣም ከፍተኛ ነበር። ኢትዮጵያ ከራስዋ ልጆች አልፋ የብዙ አፍሪካ አገሮች ወጣቶችንም በየመስኩ ታሠለጥ ን ነበር፤ ከነዚህ መሀል በየአገሮቻቸው ሚኒስተሮችና አምባሳደሮች የሆኑ ነበሩ።

በትምህርት የተደረገውን ከፍተኛ እርምጃ በገሃድ የሚያሳዩ ጥቂት መሥሪያ ቤቶ ች ነበሩ፤ --- የኢትዮጵያ ዓየር መንገድ፣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሚዩኒኬሽን፣ የመብራት ኃይ ል፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በኋላ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲ ቲ። በዘመኑ እነዚህ ድርጅቶች ከየትም አገር ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋር ተወዳድረው የማያሳፍሩ ነበሩ። ዛሬ እነዚህ ድርጅቶች ያሉበትን ሁኔታ እንድነግራችሁ የምትፈልጉ አይመስለኝም።

የአፄ አገዛዝ ለትምህርት ይህንን ያህል ትኩረት ቢሰጥም የትምህርትን ባሕርይ ለመገንዘብ አልቻለም ነበር፤ በመሠረቱ መማር መለወጥ ነው። የተማሩ ሰዎች በተማሩት መጠን ይለወጣሉ፤ የጥራዝ ነጠቅ መለወጥ ሳይሆን ጥልቀት ያለው ለውጥ ማለቴ ነው። በተለወጡት መጠን አካባቢያቸውን ለመለወጥ ይፈልጋሉ፤ አካባቢውን ወደተሻለ ሁኔታ ለመምራትና ለመለወጥ የሚደረገውን ማናቸውንም እርምጃ የአገዛዝ ሥርዓት አይፈቅድ ም። ስለዚህም ባስተዳደርና በልማት በኩል የተማረው ኃይል የተመኘውን ያህል መራመ ድ አልቻለም፤ በአገዛዙና በተማረው ኃይል በኩልቅራኔው ሰፊና ጥልቅ እየሆነ ሄደ። በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ የተሻለ ደረጃ የነበራት አገር በመሆንዋ ያንን ደረጃ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን እንድትገሰግስና ለሌሎች አርአያ እንድትሆን የዘመኑ ወጣት ምኞት ነበር። ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለጥቁሩ ዓለም የነጻነት ጮራና የተስፋ

አርአያ ሆና እንደኖረች ሁሉ በኢኮኖሚውም በኩል የከበረችና የበለጸገች አገር እንድት ሆን ከፍተኛ ጉጉት ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ እድገት የኤሊ ጉዞ ሆነበት። የአገዛዙ ትልቁ ድክመት ትምህርትን ለማስፋፋት ያደረገውን ጥረት ያህል የትምህርትን ውጤት ለመቀበል አለመቻሉ ነበር።

በመጨረሻም ይህ ባህላዊው አገዛዝ ሲወድቅ ኢትዮጵያ ያልፍላታል፤ የእድገት ግስጋሴዋ ይጣደፋል ተብሎ ነበር። ነገር ግን አገዛዙ ሥልጣንን ለብቻው ጨብጦ በአን ድ ሰው እጅ ለመቋጠር ሲል ሰዎች እንዲሰባሰቡና እንዲደራጁ፣ ሀሳባቸውንም በይፋ እንዲገልጹ የማይፈቅድ በመሆኑ አገዛዙም ሕዝቡም በጮሌ የበታች መኮንኖች ተጠለፉ ና የሳንድኸርስትና የሳን ሲር ምሩቅ ጄኔራሎች በነበሩበት አገርሻለቃዎችና የበታች ሹማ ምንት ነገሡባት። ስለዚህም የባሰና ለሰው ሕይወት ምንምዋጋ የማይሰጥ የጭካኔ አገዛዝ ተተካ፤ ስደት የኢትዮጵያውያን ባህል ሆነ፤ የትምህርት እድገት በጥራዝ ነጠቅ የማርክ ሲስትሌኒንስት እምነት ቀረቀዘ፤ ተጀምሮ የነበረው ከፍተኛ የእርሻ እድገት እንቅስቃሴ ተገታ፤ ጥሩምባ እየነፉ መግደልና መንጠቅ የጊዜው ባህል ሆነ።

በደርግም ዘመን ልክ እንደዘውዱ አገዛዝ ሥልጣን በአንድ ሰው እጅ ተቋጥሮና ሕዝቡ በጭካኔ ታፍኖ በማንአለብኝነት ግፉን እየተቀበለ እስቲያንገሽግሸው ድረስ ቆይቶ አል፤ በመጨረሻም 'የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ኃይል ያሸንፋል፤' በሚለው የራሱ የደር ግ መፈክር መሠረት ተገፍቶ ገደል ገባ፤ ደርግን የተካው ወያኔ ከጫካ የወጣ ጀሌ ነው፤ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ጄኔራሎች በበታቾቻቸው እንደተበለጡ ሁሉ ደርግም ከጫካ በወጡ ጀሌዎች ተበለጠ። ከአፄ መውደቅ ጋር የተጀመረው የቁልለት መንገድ ገና አላቆመም፤ ያለንበትን ሁኔታ ስናስበው ይህንን ለመገንዘብ አዳጋች አይደለም።

## 3. ያለንበት ሁኔታ

በአጭሩ በነደፍሁላችሁ ርኩስ መንፈስ በሰፈነበት ዓለም ውስጥ እንገኛለን፤ ይህ ርኩስ መንፈስ ሩቅ አይደለም፤ ደሀነታችን፣ የምኞት ባሮች መሆናችን፣ የውስጣችን መንቃት ወይም መሰንጣጠቅ ርኩስ መንፈስን ከያለበት የሚጋብዙ ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላማዊና መከራን የሚችል ነው፤ እንደኛ ደግና ትእግስተኛ ሕዝብ የለም፤ ተዘረ ፍን ብለን ሳንቆጣ፣ ተጠቃን ብለን ሳንጮህ፣ ሕጋዊ ሥርዓት ተፋለሰ ብለን ሳንበሳጭ፣ የደሀውና የሥራ አጡ ለቅሶና ብሶት ሳይሰማን፣ ሁላችንም በዕለት ተዕለት የኑሮ ግዴታ

ተጠምደን፣ ተጨንቀን ሳናስብ እንኖራለን። የተማረው ያልተማረውን፣ ያልተማረው የተ ማረውን እየናቀው፣ ወጣቱ በሽማግሌው፣ ሽማግሌው በወጣቱ፣ ሀብታሙ በደሀው፣ ደሀ ው በሀብታሙ፣ ገጠሬው በከተሜው፣ ከተሜው በገጠሬው እያመካኘ፣ ጠመንጃ ያነገተ ው  ሌጣውን ቀንበር እያሸከመው፣ ትናንት ስንሰግድለት የነበረውን ዛሬ እያዋረድን፣ ነገ የምናዋርደውን ዛሬ እያከበርን የኑሮ ግዴታችንን (ማለት በልቶ ማደርን) ብቻ ዓላማ አድ ርገን እንኖራለን። ስለነገው አንጨነቅም፤ ስለነገ የማንጨነቅበት ዋናው ምክንያት ነገን የሚያንፁትና የሚያቅዱት ጌቶች ስለሆኑ እኛን አያገባንም፤ ስለነገ አለመጨነቅ የባርያ ባሕርይ ነው። ስለዚህም ነገ የራሱን ጣጣ ይዞ ሲመጣ ራሳችንን ለአዲሱ ጣጣ ከማዘጋጀ ትና ጊዜያዊ የግል ጥቅማችንን ከማረጋገጥ ሌላ ለማሰብ ዝንባሌውም ፍላጎቱም የለንም። ‘ያለው ላይቀር ምን አታገለኝ’ የሚል ፍልስፍና ነው መመሪያችን።

የአንድ አገር ሕዝብ የአገርና የሥልጣን ባለቤትነቱን ለማሳወቅና ለመታገል ካልተ ነሣ እንዴት ያልፍለታል? ችግሩን ሁሉ በአገዛዝ እያመካኙ አምላክን፣ መላእክትንና ሰማ ዕታትን በመማፀን ብቻ መፍትሔ በመጠበቅ ሁለት ሺህ ዓመታት ሊሞላን ነው። ጸሎቱን ም የሚያሰምርልን ልብ የለንም፤ ልባችን በክፋትና በጥላቻ፣ በቂምና በምቀኝነት የተሞላ ስለሆነ የልባችንን የሚያውቅ አምላክ የአፋችንን ጸሎት የሚሰማበት ጆሮ ያለው አይመስ ለኝም። በቀን ብዙ ጊዜ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል እያለ የሚጸልየው ሁሉ የም ሕረትና የይቅርታ አቅዋም በሚያስፈልግበት ጊዜ አካሉ እየተንቀጠቀጠ አንደበቱ የበቀል ን እሳት ይተፋል፤ እንኳን የቅርቡን የምዕተዓመታት ታሪክን እያስታወሰ ለበቀል ጦር ይሰ ብቃል። ስለዚህ ለጸሎትም ቢሆን ልባችን ንጽሕና ይጎድለዋል፤ አገራችን በመንፋሳዊነት ም የከሰረች ነች። መንፈሳዊነትን በሃይማኖታዊ ትርጉሙ ብቻ አንውሰደው፤ እኔ የምጠ ቀምበት ለእውነት፣ ለነጻነትና ለፍትሕ፣ ለእኩልነትና በአጠቃላይ ክፋውንና በጎውን ለም ንለይባቸው የኅሊና ተግባሮች ሁሉ ጭምር ነው።

በዚያ ላይ ጎመን በጤና በሚል ሰንካላ ፍልስፍና ተመርዘናል፤ ፍርሃት ወኔአችንን ገድሎታል፤ ኢትዮጵያውያን የምንላቸው የእውቀትና የሀብት ባለቤት የሆኑትን ብቻ ቢሆ ን እኔ በበኩሌ አገዛዙ የሚገባቸው ነው ለማለት አያዳግተኝም ነበር፤ ነገር ግን ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በችግርና በችጋር እየተጠበሰ የሚኖር ነው፤ ለእሱ፣ በጭቆናና በብዝበዛ ስር በችግር ተወልዶ በችግር ለሚሞተው አገዛዝ ጸሩ ነው። የሀብትና የእውቀት ባለቤቶች ምርጫቸው ብዙ ነው፤ከተገነዘቡት ባላቸው መጠን ግዴታ

ቸው ወይም ኃላፊነታቸው ከባድ እየሆነ ይሄዳል፤ይህንን ግዴታ አለመቀበላቸው ካላቸው የምርጫ ብዛት ጋር በጭቆና ስር መውደቃቸው የሚታዘንላቸው አያደርጋቸውም። ማኅበ ረሰቡ ከነዚህ ክፍሎች የሚጠብቀውን የአለኝታነት፣ የመከታነትና የአመራር በረከት ገና አላገኘም። ለማኅበረሰባችን መንፈሳዊ ውድቀት አንዱና ዋናው መግለጫ የህብትና የእው ቀት ባለቤት የሆነው ክፍል ግዴታቢስነት ነው፤ ከተመቸውና በኢትዮጵያ መጠቀም ከቻ ለ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለግዴታ መኖርን፣ ካልተመቸው በሌላ አገር ሄዶ መኖርን እንደ አማራጭ ይዞ ያለ ነው። በሌላ አነጋገር አንድ እግሩን በፈረንጅ አገር አንድ እግሩን በኢ ትዮጵያ አንፈራጥጦ የሚኖር ነው፤ እንደአንድ አገር ሕዝብ የብዙኃኑ ስቃይና ብሶት እን ዲጋባብንና እንዲሰማን ኅሊናችን አስገድዶን ኢትዮጵያ ለእኛ የወፍራም እንጀራ ምንጭ ብቻ ሳትሆን እኛም የርስዋ እንጀራ ምንጭ መሆናችንን መቀበል ገና አልቻልንም። በራሳ ችን ዓይን ያለውን ጉድፍ ሳናወጣ አገዛዙ ላይ ጣታችንን መጠቆሙ ብቻ የትም አያደር ሰንም።

የመንፈስ ደካሞች በመሆናችንም አሁንም የምንኖረው እንደተለመደው ከእኛ ቁጥጥር ውጭ በሆነ የአገዛዝ ሥርዓት ስር ነው። የአገዛዝ ሥርዓቱ መሠረታዊ ባሕርይ ሁሉንም ነገር ለብቻ በሞኖፖል መያዝና ሁሉንም ነገር መቆጣጠር ነው፤ የአገር ሥልጣ ንን ለብቻው፣ የሀብት መሠረት የሆነውን መሬትን ለብቻው፣ የሕዝብ የዜና ማሰራጫዎ ችን ለብቻው፣ የአገዛዝ ሥርዓቱ ራሱ የፖሊቲካና የኢኮኖሚ ጥገኛ ሆኖ ሳለ የአገሩን በለሀብቶች በጥገኝነት እየፈረጀ ለማሳፈርና እድገታቸውን ለመግታት የሚሻው ጥገኝነትን ም በሞኖፖል ለመያዝ ይመስላል። በዚያ ላይ ሥርዓቱ የዜና ማሰራጫ፣ የዜና ወኪል፣ የንግድና የኢንዱስትሪ፣ የቲአትር፣ የማስታወቂያና የማሳተሚያ ድርጅቶች ቢያንስ የእጅ አዙር ባለቤት ሆኖ ሌሎች ባለሀብቶች የማያገኙትን ዕድልና ድጋፍ በማግኘት ከውድድር ውጭ ያደርጋቸዋል፤ በማኦኢሰቶች አነጋገር ይህ የቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ነው።

ኢትዮጵያውያን ሁሉ ባይስማሙበትምና አፄ ኃይለ ሥላሴ 'ለምንወደው ሕዝባችን እንዳሉት ባይሆንም፣ ለምንገዛቸው ጎሣዎቻችን በሚል መንገድ የተሰጠና መነሻ ሆኖ ሊያስሠራ የሚችል ሕገ መንግሥት ለወጉ አለ። ዛሬ ጥያቄው ሕገ መንግሥቱ ጥሩ ነው? ወይስ መጥፎ? የሚል አይደለም፤ ጥያቄው ሕገ መንግሥቱ ነፍሱ አለ ወይ? ነው። አገዛ ዙራሱ በገሃድ ያለምንም ሐፍረት የሕገ መንግሥቱን ጥርስ ሲያረግፈው እያየን ነው። እንዳሁኑ የአገዛዝ ሥርዓት ፍትሕን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ስር ያደረገ ከዚህ በፊት

አልታየም። በአሁኑ አገዛዝ ደሀዎች ሴቶችና ወንዶች ልጆች ከየመንገዱ ሌሊት እየተለ ቀሙ ከከተማ ውጭ ስንት ጊዜ ለጅብ ተጣሉ? በቅርቡ አንዱን ጋዜጠኛ እንደአባብ ራሱ ን ቀጥቅጠው ከድልድይ ወደወንዝ ወረውሩት፤ ዛሬ በሕግ አምላክ ማለት ትርጉም የለ ውም። ስንት ሺህ ሰዎች ናቸው ፍርድ ቤት እንኳን ሳይቀርቡ በእስር ቤት አሥር ዓመት ያለፋቸው? ስንት መቶ ሰዎች ናቸው ተገድለው ደማቸው ደመ ከልብ ሆኖ የቀረው? ስን ት ሰዎች ናቸው በጥራጣሬ ብቻ በእስር ቤት የሚማቅቁት? ስንት ሺህ ሰዎች ናቸው ከኤ ርትራ ተፈናቅለው ከአሥር ዓመት በላይ ከአንድ መጠለያ ወደሌላ መጠለያ እየተባረሩ የሚኖሩት? ስንት ልጆች በየመጠለያው እየተወለዱ በየባቡር መንገዱ ላይ ያድጋሉ? ስንት ሺህ ሰዎች በኤርትራ ጦርነት ምክንያት ከየቤታቸው ተፈናቀሉ? ስንት ሺህ ሰዎች በጎሣ ምክንያት ተፈናቅለው በችግር ይኖራሉ? አሁን ደግሞ ስንት ሺህ ሰዎች ከጂቡቲ ተፈና ቅለው መጥተዋል? የመንም ኢትዮጵያውያንን እያባረረች ነው ይባላል፤ እነዚህ ሰዎች ሁሉ አገርና መንግሥት አላቸው? ወገን አላቸው?

አሁን ያለንበት የአገዛዝ ሥርዓት የደርግ የባሕርይ ታናሽ ወንድም ነው፤ በደርግና በወያኔ አገዛዞች መሀከል ያለው ልዩነት የጌቶቻቸው የባሕርይ ልዩነት ብቻ ነው። የደር ግ አገዛዝ አፍአዊ ገጽታውን የሶሺያሊስት ቀለም እንዲቀባ የተገደደውን ያህል፣ የወያኔ አገዛዝም አፍአዊ ገጽታውን የዴሞክራሲ ቀለም እንዲቀባ ተገደደ። ጉልቻውና ቀለሙ ተለዋወጠ እንጂ ማገዶውና የሚጠበሰው ያው ነው። የበላውና የጠገበው ሲሄድ የራበው ና ሁሉ-ብርቁ ይተካል፤ በሁለቱም ላይ ቢሆን ራስን መጠራጠር፣ በጎ ፈቃድና መንፈሳዊ ወኔ የለም። በሁለቱም ላይ ጎልቶ የሚታየው በተለያየ መንገድ ከእነሱ የሚበልጡ ሰዎች በአገር እንዳይኖሩ ነው። ወደአውሮፓም ሆነ ወደአሜሪካ፣ ወደአውስተራልያም ሆነ ወደ አረብ አገሮች ስደትን የኢትዮጵያውያን ባህል ያደረጉ አገዛዞች ናቸው።

## 4. **የያዝነው አቅጣጫ የት ያደርሰናል**?

ከተለያየ የትምህርትና የሥራ መስክ የመጡ ቢሆኑም ከዚህ በፊት የተናገሩት ሁሉ በአንድ ነገር ላይ ይስማማሉ፤ --- አሁን በተያዘው መንገድ መቀጠል አንችልም። የያዝነው መንገድ ወደ'ከፋ ዕድል'፣ ወደ'መዓት'፣ ወደ'ውድቀት' የሚያመራ መሆኑ ተገ ልጾአል። ለእኔ የአዘቅቱ መንገድ የሚታየኝ እንደሚከተለው ነው፤ በሸምበቆ አጥር የተለ ያዩና የሚተራመሱ ጎሣዎችን ጭኖ የሚከንፍ ባቡር ይታየኛል፤ ነጂው መትረየሱን ይዞ

ፊቱን አዙሮ የተቀመጠው ወደሚነዳበት አቅጣጫ ሳይሆን ወደተሳፋሪዎቹ ነው፤ ተሳፋሪ ዎቹ የሚያዩት ወደፊት ነው፣ ነጂው የሚያየው ወደኋላ ነው፤ ስለዚህም ነጂው ገደሉን ስለማያይ ይበልጥ የሚያስፈራው የተሳፋሪዎቹ ትርምስ ነው፤ ተሳፋሪዎቹን የሚያስፈራቸ ው የሚታያቸው መትረየስና ገደል ነው። በባቡሩ ውስጥ ያሉ ተሳፋሪዎች ሁሉ በባቡሩ ፍጥነት ላይም ሆነ አቅጣጫ ላይ ምንም ዓይነት ቁጥጥር የላቸውም፤ የባቡሩ ነጂ ተሳፋ ሪዎቹ የሚያዩትን አያይም፤ እንዲነግሩትም አይፈልግም፤ የነጂውና የተሳፋሪዎቹ አስተሳሰ ብ ለየቅል ነው፤ አይነጋገሩም፤ ተሳፋሪዎቹ በዝምታ ነጂው የማያየው ገደል ውስጥ ለመ ግባት ቆርጠዋል፤ ባቡሩን አቁም ብለው ቢጮሁ መልሱ መትረየስ መሆኑን ያውቃሉ፤ በዝምታ አብሮ ገደል መግባት ነው። በዚህ አጣብቂኝና የፍርሃት ቆፈን ተይዘናል፤ ከተረ ዳንለት ነጂውም አጣብቂኝና የፍርሃት ቆፈን ውስጥ ነው፤ ነጂውና ተሳፋሪዎቹ ካልተነጋ ገሩ ባቡሩም፣ ተሳፋሪዎቹም፣ ነጂውም ከገደሉ ማምለጥ አይችሉም።

እንግዲህ መሣሪያ የያዘውም ይፈራል፤መሣሪያ ያልያዘውም ይፈራል ማለት ነው፤ የሁለቱም ጠላት አለመተማመንና መሣሪያው ነው። አለመተማመንን ሳናጠፋ መሣሪያውን ማጥፋት አንችልም፤ ሳንነጋገር አለመተማመንን ማጥፋት አንችልም፤ ልባችን ከቂምና ከበቀል ካልፀዳ ተነጋግረን መግባባት እንችልም። ባቡሩ እውር ድንብሩን እየሄደ ገደል የሚገባው ለዚህ ነው።

የባቡሩ ገደል መግባት የአደጋው መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ ይሆናል የሚል ግም ት የለኝም፤ አደጋው የጎሣ ትርምስና የቂም መወጫ ሁኔታን ይፈጥራል። ለብዙ ምዕተዓ መታት ወደኋላ ሄደን ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር እንሰለፋለን። የያዝነው መንገድ ወደዚህ እንደሚያመራ ለእኔ ግልጽ ነው። ይህንን የሚጠራጠር ትንሽ ያስብበት፤ ለሌሎ ች የተዘራው የጎሣ መርዝ ባልታሰበበት መንገድ ሄዶ በኤርትራና በትግራይ ተወላጆች መሀከል የከፋ መልኩን ማሳየቱ የሚያሳዝንና የመርዙንምም ጠምዛዛነት የሚያመለክት ነው፤ የዚህ ጦስም የትግራይ ተወላጆችንም በመከፋፈል ላይ ነው። ኦነግ ጎልቶ የሚታይ ቢሆንም በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በማቆጥቆጥ ላይ ያለው ጎሠኛነት ጉዳዩን ለሚከ ታተሉ ሁሉ ግልጽ ነው። በጎሠኛነት ተኮትኩተው ያደጉ ልጆች እየደረሱ ነው፤ አንድ ትውልድ ሊሆን ምንም ያህል አልቀረውም። ብዙዎቻችንን የሚያሳስበን የደህነቱና የችጋ ሩ ጉዳይ ነው፤ የኢትዮጵያን ህልውና ጉዳይ ባንረሳውም አደጋውን ላለመቀበል አእምሮ አችንን የምንጋርደው ይመስለኛል፤ ጭንቅላታችንን አሸዋ ውስጥ ቀብረን የምንፈልገውን

*መመኘቱ ብቻ አቅጣጫችንን አይለውጠውም። እኔ የማውቃትና አገሬ የምላት ኢትዮጵያ አሁንም በከፊል የለችም፤ በያዝነው መንገድ ከቀጠልን ደግሞ ያሁንዋም ኢትዮጵያ* 2020 *የምትደርስ አይመስለኝም። በያዝነው መንገድ ከቀጠልን የብዙ የአፍሪካ አገሮች ሁኔታ ውስጥ መግባት የማይቀር ነው፤ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በጥያቄ ምልክት ውስጥ መግባትዋ የሚቀር አይመስለኝም፤ ከዘመነ መሳፍንት የባሰና አስከፊ ሁኔታ እንደሚያጋጥመንና በሆነ ባልሆነው መከሳከሳችን ይቀራል ብዬ አልገምትም።*

*የወደፊቱ ግጭት ከአሁን በፊት ከለመድነው በጣም የተለየ ይሆናል፤ እስከዛሬ የምናውቀው ግጭት በአፈንጋጭ የማኅበረሰቡ ክፍልና በአገዛዙ መሀከል ነበር፤ ቀደም ሲል እንደተናገርሁት ደርግ ራሱ ባወጣው 'የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ያሸንፋል፤' በሚለው ሕግ ወደቀ፤ ወያኔም ራሱ የጠነሰሰውና ሕጋዊ ያደረገው ጎሠኛነት የሚፈጥረው ግጭት እንደበፊቱ በአገዛዝና በአፈንጋጭ ቡድን መሀከል ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ጎሣዎችም መሀከል ይሆናል። በጎሠኛነት ተኮትኩቶ ያደገ ትውልድ በማኮብኮብ ላይ ነው ብያለሁ። ዛሬ በትግራይና በኤርትራ ተወላጆች መሀከል ያለው ስሜት ነገ በሌሎች መሀከል ይከሰታል። በተነጠቁት መሬት የተነሣ ወሎና ጎንደር ውስጥ ያለው የታፈነ ንዴት ቀላል አይደለም፤ አፋር ተከፍሎና ታፍኖ አይኖርም፤ ኦነግ እየተዋጋ ነው፤ ኦጋዴን ለመገንጠል ይችላል የሚል ማደፋፈሪያ ተሰጥቶታል፤ ሌላው በየጎራው እያብላላው ነው፤ የጎሣው ግጭት የሚፈጥረው ትርምስና መተላለቅ ከጀመረ በራሱ ኃይል እየተቀጣጠለ ስለሚስፋፋ ለማቆም አስቸጋሪ ይሆናል፤ ስለዚህም ሰላም ይኖራል ብዬ አልገምትም። አዘቅቱ የከፋና የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ አይቶት የማያውቀው፣ ደህነትና ችጋር ጭካኔን እየወለደ፣ በጎሠኛነት ሞተር እየተነዳ፣ በጥላቻና በቂም የታወረ ክፋት በገሃድ የሚወጣበት መተላለቅ ነው።*

*በዚህ መተላለቅ ከአካባቢያችን የሚረዱን አይጠፉም፤ በአለፉት ዓመታት ከሶማልያና ከኤርትራ ጋር የተደረገው መዳማት፣ ከጂቡቲ ጋር የተከሰተው አለመግባባት፣ በአንድ በኩል ከአሜሪካ ጋር፣ በሌላ በኩል ከሱዳን ጋር የተደረገው ሽር-ጉድ የሚከተሉትን ዓመታት ለኢትዮጵያ የሚመቹ አያደርጉም። እኔ እንደምገምተው ሁሉም የተነበየው አዘቅት ወይም መዓት አፋፍ ላይ በ*1997 *መጨረሻ እንደርሳለን። <u>አዲስ ኢትዮጵያ የምትወለደው ከኤርትራ እስከቦረና ከጋመቤላ እስከጂጂጋ ሁሉም በአንድ ጊዜና በአንድ ላይ በሚሰማው የጭንቀት ምጥ ይሆናል</u>። ሕገ አራዊት የሚያደርሰን እዚህ ነው። የሰው ልጅ*

አእምሮ ውስብስቡን የኑሮ ገመድ ሲገምድና ሲፈታ እኛ ገና ከቀላሉ የማስፈራራትና የጡንቻ ዘዴ አልወጣንም፤ በማስፈራራትና በጭቆና የጨቋኙም የተጨቋኙም አእምሮ ደንዝዞ፣ መንፈስም ታምሞ፣ በደነዘዘ አእምሮና በታመመ መንፈስ ትርጉም ያለው ሥራ ለራሳችንም ሆነ ለማኅበረሰባችን ለማበርከት አንችልም።

እንደምትገምቱት ይህንን መናገር ቀላል አይደለም፤ እስካሁን ድረስ ሦስት አገዛዞ ች በውርደት ሲወድቁ አይቻለሁ፤ የሁለቱ አገዛዞች መውደቅ በቅድሚያ ታውቆኝ በአደ ባባይ ተናግሬ ነበር። የአሁኑ አገዛዝ በዓይነቱ በጣም የተለየ ነው፤ ራሱን ለማረም በጊዜ ው ካልጣረ አወዳደቁም የተለየና አገሪቱንም የሚያጠፋ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ባሕሩ እንዳለው ኢትዮጵያ የተአምር አገር ነች፤ ለለቀላት ሲባል ነፍስ ዘርታ ትነሣለች። እንደ ዚያ ከሆነ ደስታው የሁላችንም ነው። በተአምር ባምንም እጆቻችንን አጣምረን በመቀ መጥ ከአንዣበበው አደጋ እናመልጣለን ብዬ ግን ለላስብም።

## 5. አደጋውን ለማስቀረት ምን ማድረግ አለብን?

ይህንን ጸሑፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ከፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በቅርቡ የሚታተም መጽሐፍ ረቂቅ ደርሶኝ እያነበብሁ ነበር፤ ስለደቂቀ እስጢፋኖስበአሥራ አምስተኛው ምዕተዓመት መጀመሪያ ላይ የሆነውን ከግዕዝ የተረጎመው ነው፤ ከተጻፈ ስድስት መቶ ዓመታት የሆነው ነገር ሁሉ ዛሬም የሚሆን ነው፤ የሚያሳዝንም የሚያስደንቅም ነው፤ በሥልጣን ላይ ያሉት ሰዎች የሀሳብ ልዩነትን መቀበል የማይችሉ መሆናቸውና እንዲህ ያሉትን ሰዎች በተለያየ መንገድ ማሰቃየታቸው፣ የማሰቃያው መንገድም ብዛቱ እንዳለን ምንም ሳንለወጥ መቆየታችንን በግልጽ ያመለክታል።

ለእኔ እንደሚታየኝ አቃለልከው ካላላችሁኝ ታሪካዊ ችግሮቻችን ሁለት ብቻ ናቸ ው፤ አንደኛ፣ በረጅሙ ታሪካችን ውስጥ የምናየው በሕገ አራዊት መመራትን ነው፤ ከኃ ይል የተሻለ የመተዳደሪያ ዘዴ አልፈጠርንም፤ የበላይና የበታች በመሆን ባለመብትና ባለ ግዴታ እየተለየ ጌታና ሎሌ በመሆን አጉል መቻቻል እንጂ በእኩልነት ላይ ለተመሠረተ ግንኙነት የሚሆን ዘዴ አላገኘንም። ሥልጣንን መግራት ሳንማር 1996 ደርሰናል፤ ሥልጣን ን መግራት የሥልጡን ሕዝብ መታወቂያ ምልክት ነው፤ በሕገ አራዊትና በጉልበት እየተ ገለባበጥን እንቃጠላለን። የእድገትና የልማት አንዱ ምሥጢሩ ሥልጣንን መግራት ነው፣ ሥልጣንን በእኩልነት ሕጋዊ ማድረግ ነው።

ሕገ አራዊትን መመሪያችን በማድረጋችን ነው በአጠቃላይ ባህላችን የነፍጠኛነት ና የጀብደኛት የሆነው፤ ጠመንጃ ተይዞ በፉከራና በሽለላ ታጅቦ፣ ጀግና፣ ገዳይ በመሆን ነው 'እኔ ያንተ አሽከር ያንተ ቡችላ' የሚባልለት፤ አሁን ደግሞ ማጅራት መቺ፣ አከርካ ሪት ሰባሪ ሆኖ በሕገ አራዊት ለሚያደናብረው ነው አሽከርነት የሚያድረው፤ አሽከር ዛሬ ስሙ ተለውጦ ካድሬ ሆኖአል እንጂ እዚያው ነን። በባህላችን ብዙ መሳፍንትና መኳንንት ስለነበሩ አሽከር ምርጫ ነበረው፤ ዛሬ ጌታው አንድ ብቻ በመሆኑ ምርጫም የለም፤ ዘመናዊነቱና ለውጡ እስከዚህ ድረስ ነው። የምናየውና የምንሰማው ያንኑ የለመ ድነውን ጭፍን እልህ ነው። የጂቡቲው ፕሬዚደንት ጉሌድ ዲፕሎማሲያዊ ቋንቋውን ጥለው 'የኢትዮጵያና የኤርትራ ሰዎች ከሚገባው በላይ ቁጡና ጠበኛ'[1] ናቸው ብለው መናገራቸው በሕገ አራዊት ላይ የተመሠረተው አገዛዝ ድንበር አልፎ መታወቁን የሚያ መለክት ነው።

ሁለተኛው ችግራችን ሥልጣንና ሕገ ኀልዮት አለመተዋወቃቸው ነው፤ ሕገ አራዊ ት አይሎ ነው እንጂ ሕገ ኀልዮት ለኢትዮጵያ ባዕድ ሆኖ አይደለም፤ የፈላስፋዎቹን የዘ ርዓ ያዕቆብንና የወልደ ሰንበትን ጽሑፎች ያነበበ ሁሉ እንደሚረዳው፣ አሁን ደግሞ ፕ ሮፌሰር ጌታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ከግዕዝ ወደአማርኛ እየተረጎመ የሚያሳትማቸው መጻ ሕፍትም እንደሚያሳዩን ማሰብ በጡንቻ እየተጨፈለቀ ደብዛው እንዲጠፋ ተደረገ እንጂ በአዲስ መንገድ ማሰብ የሚችሉ ሰዎች በየጊዜው ብቅ ብቅ ብለው እንደነበረ እናያለን። የሀሳብ ልዩነት የማይፈቀድና ለከባድ አደጋ የሚዳርግ መሆኑ ቢያንስ ከአሥራ አምስተኛ ው ምዕተዓመት መነሻ ላይ እንደጀመረና ለስድስት መቶ ዓመታት ቆመን እንደቀረን ያሳ የናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጦርነት ሲሉት ፈንቅሎ የሚወጣውን ያህል ለሰላማዊ ትግል አንድነቱን ቢያሳይ ኢትዮጵያን ከታሪካዊ ችግሮችዋ መገላገል ይቻል ነበር።

ከኤርትራ ጋር ለተደረገው የወንድማማች ጦርነት የሀብትና የእውቀት ባለቤቶች ያደረጉት ከባድ አስተዋጽኦ የሚያስደንቅ ነው፤በእነሱ አመራርም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች ለባድመ ተማገዱ፤ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል ግን ከዩኒቨርሲ ቲ ተማሪዎች በቀር የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣውን ለማሳየት እንኳን አልሞከረም፤ ለሞት በቀላሉ እንነዳለን፤ ለሕይወት ግን በሰላም ለመታገል እንፈራለን፤ ዛሬም የባድመ ነገር የሚያንገበግባቸው ብዙ ናቸው፤ በአንጻሩ ደግሞ የአሰብ ጉዳይ የሚያቃጥላቸው ብዙ

[1] አዲስ አድማስ ጋዜጣ ጥቅምት 21/96

ናቸው፤ የባድመ ተቆርቋሪ የአሰብ ተቆርቋሪው ንዴት የሚገባው አይመስልም፤ እንዲሁ ም ለዚያኛው፤ ለቁጣችንም ሆነ ለትእግስታችን ሚዛን የለንም፤ ይህ ሁሉ የሚያሳየው ሕገ አራዊት በሕገ ኀልዮት ላይ ያለውን የበላይነት ነው። ይህ መለወጥ አለበት፤ እኛ መለወጥ አለብን፤ እኛ ራሳችንን ሳንለውጥ ምንም ነገር መለወጥ አንችልም።

ለጦርነት የምናሳየውን የጋለ ስሜት ለሰላማዊ ትግል አናሳይም፤ ሰላማዊ ትግል ወይም ፖሊቲካ ገና አልገባንም፤ ደርግ ሰላማዊ ትግሉን ወደሶሺያሊስት የመደብ ትግል ለወጠው፤መደብ በሌለበት አገር። ወያኔ ደግሞ በልጅነት ጥበቡ የሰላሙን ትግል መሠረ ታዊ የሰው ልጅን አንድነት በሚቃረንና ወደድርድር በማይቀርብ የጎሣ ትግል ለወጠው። የደርግ ሶሺያሊስት ትግል ሁሉንም ደሀ በማድረግ መፍትሔ ለማግኘት ይችል ነበር፤ ሁሉንም ሀብታም ለማድረግ እስቲችል ድረስ። የወያኔ እልህ ግን ከመበታተን ሌላ መፍ ትሔነት ያለው አይመስልም። የሚደንቀው የጎሣ ትግሉ በእያንዳንዱ በአመራር ደረጃ ባለ ሰው ላይ የፈጠረውን የውስጥ ቅራኔ እንኳን መገንዘብ አለመቻሉ ነው። እንኳን ራቅ ካሉ ጎሣዎችና በጣም በተቀራረቡትም በትግራይና በኤርትራ መሀከል መደባለቅ ችግር እየፈጠረ እናያለን። መበታተኑም ወግና ሥርዓት ባለው መንገድ እንደማይሆን ባድመ እያ ስተማረን ነው፤ (ገና ጥንት አብርሃም ሊንከልን አንድ ቤት ውስጥ ሆነው ለመፈጸም ያል ተቻለውን ውል ከተለያዩ በኋላ ያስቸግራል ብሎ ነበር፤) በደቡብም በየጊዜው የሚከሰቱ ግጭቶች የወደፊቱን ችግር እያመላከቱን ነው። መበታተኑም ቢሆን ሰላማዊ ላይሆን ይችላል የሚል ስጋት አለኝ።

በሕገ ኀልዮት የምንመራ ቢሆን ለማናቸውም ዓይነት እድገትና ልማት የሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነት ወይም ዴሞክራሲ የሚባለው ወሳኝ መሆኑን መረዳት አያዳግተንም ነበር፤ የተዳፈነውና የታመቀው የሕዝብ የአካል፣ የአእምሮና የመንፈስ ኃይል ሊወጣ የሚችለው ሕዝቡ ነጻ ሲወጣና ሥልጣንን ተረክቦ በራሱና በሕግ በመተማመን ለኑሮውና ለሕይወቱ ባለቤት የሚሆንበት ሁኔታ ሲፈጠር ብቻ ነው። በኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበ ር፣ በኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር፣ በኢትዮጵያ ነጻ ጋዜጠኞች ማኅበርና በከተማና በገ ጠር ቀበሌ ማኅበራት ላይ የሚደረገው አፈናና ጫና ዴሞክራሲን በኢትዮጵያ ለመገንባት አይረዳም። ዴሞክራሲ የሚገነባው በልበሙሉ ዜጎች ነው፤ ማስፈራራትና ማስሸበር ቀር ቶ የሥልጣን ትግል ሁሉ ሰላማዊና ሕጋዊ ሲሆን ነው። በተጨማሪም የዴሞክራሲ ጥቅ

ም እያንዳንዱ ዜጋ፣ ሕዝቡም በአጠቃላይ ለራሱ ኑሮና ለአገሩ እድገት ኃላፊነትን እንዲሸከም ማድረጉ ነው። በአገዛዝ ስር ያለ ሕዝብ ነጻነትም ኃላፊነትም የለውም።

የኢትዮጵያን ህልውና ጠብቀን የሚቀጥለውን ትውልድ ከደህነት፣ ከችጋር፣ከጦርነትና ከእርስበርስ እልቂት የሚያድነው የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትና የሕግ የበላይነት በሚቀጥለው ምርጫ መደምደሚያ ያገኛል ብለው የሚያምኑ ሰዎች ያሉ ይመስለኛል። በምኞትም ሆነ በተስፋ ደረጃ ከእነሱ ጋር አቆማለሁ። ግን ከፍተኛ ጥርጣሬ አለኝ። የዛሬ አሥራ ሁለት ዓመት ግድም በየዋህነት አንድ ነገር ተናግሬ ነበር፤ ወያኔ ትክክለኛ ምርጫ አካሂዶ ከአሸነፈ ጥሩ፣ ካላሸነፈም ለኢትዮጵያ አዲስ የዴሞክራሲ ምዕራፍ ከፍቶ በክብር የሚቀጥለውን ምርጫ ይጠብቃል ብዬ  ነበር፤ ይህ ምኞት ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ነበር። በኋላ እንደተማርሁት እንኳን በዚያን ጊዜና ለምንጊዜም ሥልጣንን እንደማይለቅቁ ነው። ሌላውን ሁሉ ትተን ለአገርና ለወገን የሚያስብ ሰው ከኤርትራ ጦርነት በኋላ ስሕተትን በማረም ብዙ ጉዳዮችን ማስተካከል ይቻል ነበር፤ በድንበሩ ምክንያት የተነሣውንም ውዝግብ በአዲስ መንገድ መፍታት ሳይቻል አይቀርም ነበር።

በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያንዣበበውን አስከፊ ችግርና የአገሪቱንም ህልውና የሚፈታተነውን ሁኔታ እያቃለሉ መገመቱ በሁሉም በኩል ቁርጠኛነት እንዳይኖር ያደርጋል፤ እውነቱ አስደንጋጭ ቢመስልም ኮስተር ብለን እንድንዘጋጅ ይረዳናል። የአእምሮና የመንፈስ ዝግጅትም ግዴታችን ይሆናል፤ አእምሮአችንንና ልባችንን ማፅዳትና መተማመን ያሻናል፤ ጠባችን የሀሳብ ልዩነት አይደለም፤ አለመተማመንና መፈራራት ነው። መንገድ ፈልገን እንተማመን፤ እኛ በሰላም ተከባብረን ሀሳቦቻችን ይጋጩ፣ ይፋጩ፤ በሚወጣውም ብርሃን አገራችንን እንገንባ። የአገራችን ጥሩ ባህል ስለነበረው እርቅ አለቃ አያሌው ታምሩ የሚከተለውን ጽፈዋል፤ ---

> ወንድማማቾች በማይገባ ነገር ተጣልተው በሃሳብ ተለያይተው፣ የማይግባቡና የማይስማሙ ከዚያም አልፎ ነገራቸው ከዳኛ የሚያደርሳቸው አንዱ በአንዱ ላይ ክፉ ለመሥራት የሚገፋፋቸው ሆኖ ሲገኝ ከፀቡ አግባብ የሌላቸው ወዳጆች፣ ጓደኞች፣ ባልንጀሮች፣ ሽማግሌዎች በመሐከል ገብተው ማልደው በፍቅር ተቆጥተው ወይም አባብለው ለዕርቅ ቢያደርሱአቸው

ሲፈርስ የነበረ ቤት ይታነጻል፤ የፈሰሰ ደም ይደርቃል፤ ነባር ቂም በቀል ይርቃል።[2]

መንፈሳዊ ወኔውን አግኝተን ይህን ለማድረግ ከቻልን ኢትዮጵያን ከአደጋ ማውጣት ብቻ ሳይሆን የምንኮራባትና የምንመካባት አገር ልናደርጋት ችሎታው አለን፤ ከዱሮ ጀምሮ የነበረኝ እምነት ኢትዮጵያ ትክክለኛ መንግሥት ስታገኝ በአንድ ትውልድ የአፍሪካ ጃፓን ለመሆን ትችላለች። ሆኖም ጊዜ የለንም፤ ዛሬ መጀመር አለብን።

[2] አለቃ አያሌው ታምሩ፣ ምልጃ፣ እርቅና ሰላም፣ አዲስ አበባ፣ 1992